የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አራተኛ ዓመት ቁጥር ፶፬
አዲስ አበባ–ሰኔ ፳፫ ቀን ፲፱፻፺

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

4th Year No. 54
ADDIS ABABA - 30th June, 1998


## ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፩፻፳፬/፲፱፻፺ ዓ.ም.
ለትምህርት ልማት ፕሮግራም ከፊል ማስፈጸሚያ ከዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ................................ ገጽ ፯፻፺፮


## CONTENTS


Proclamation No. 124/1998
International Development Association Credit Agreement for Partly Financing the Education Sector Development Program Ratification Proclamation ................................................ Page 796


## አዋጅ ቁጥር ፩፻፳፬/፲፱፻፺

### በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

ለትምህርት ልማት ፕሮግራም ከፊል ማስፈጸሚያ የሚውል መጠኑ ኤስ.ዲ.አር ፸፬ ሚሊዮን ፫፻ሺህ (ሰባ አራት ሚሊዮን ሦስት መቶ ሺህ ኤስ.ዲ.አር) የሆነ ገንዘብ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር መካከል እ.ኤ.አ. ጁን ፬ ቀን ፲፱፻፺፰ ዋሽንግተን ዲ.ሲ. የተፈረመ በመሆኑ፣

መሠረታዊ የኢኮኖሚ ዓለምአቀፍ ውሎች ተፈጻሚ ከመሆናቸው በፊት መጽደቅ ስላለባቸው፣

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፳፫ ቀን ፲፱፻፺ ዓ.ም. ባደረገው ስብሰባው ያጸደቀው ስለሆነ፣

በሕገመንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## PROCLAMATION NO. 124/1998

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE CREDIT AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION

WHEREAS, a Development Credit Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the Intrnational Development Association provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Credit amount of SDR 74,300,000 (seventy four million three hundred thousand Special Drawing Rights) for partly financing the Education Sector Development Program, was signed in Washington D.C, on the 4th day of June, 1998;

WHEREAS, basic economic international agreements have to be ratified prior to entry into force;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Credit Agrement at its session held on the 30th day of June, 1998;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 sub-Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለትምህርት ልማት ፕሮግራም ከፊል ማስፈጸሚያ ከዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩፻፳፬/፲፱፻፺" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ "የብድር ስምምነት" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር መካከል እ·ኤ·አ· ጁን ፬ ቀን ፲፱፻፺፰ በዋሽንግተን ዲ·ሲ· የተፈረመው ቁጥር ፫ ሺህ ፸፯ ኢ.ት· የብድር ስምምነት ነው።

፫· የገንዘብ ሚኒስትር ሥልጣን

የገንዘብ ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ኤስ·ዲ·አር ፸፬ ሚሊዮን ፫፻ሺህ (ሰባ አራት ሚሊዮን ሦስት መቶ ሺህ ኤስ·ዲ·አር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

፬· አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከሰኔ ፳፫ ቀን ፲፱፻፺ ዓ·ም ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ሰኔ ፳፫ ቀን ፲፱፻፺ ዓ·ም

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፕሬዚዳንት

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Credit Agreement for partly Financing the Education Sector Development Program Ratification proclamation No. 124/1998."

2. *Definition*

In this proclamaiton "Crdit Agreement" Means the Credit Agreement No. 3077 ET. signed in Wahsington DC on the 4th day of June, 1998 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association.

3. *Power of the Minister of Finance*

The Minister of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the credit amount of SDR 74,300,000 (seventy four million three hundred thousand Special Drawing Rights) in accordance with the terms and conditions set forth in the Credit Agreement.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall come into force as of the 30th day of June, 1998.

Done at Addis Ababa, this 30th day of June, 1998.

NEGASO GIDADA (DR.)

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE